# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 329 ነሃሴ 23 2006 ገጽ

ሶስቱ ድርጅቶች ለማድረግ በወሰንነው ውህደት የዚህ የአገር አድን ሠራዊት ምሥረታን ጀምረናል። ስለኢትዮጵያ እና ሕዝቧ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ ላለ ማንኛውም የኅብረተሰብ ክፍል ደህንነት ያገባናል የምትሉ ወገኖቻችን ሁሉ በዚህ አገር አድን ሠራዊት ምሥረታ ላይ እንድንነጋገር አበክረን እንጠይቃለን።

የኢትዮጵያ ሕዝብም የትብብሩ መንፈስ አገርን የማዳን ግብ ያለመ መሆኑን በመገንዘብ ከተባበረው ድርጅት ጎን እንዲቆም ጥሪ እናደርጋለን።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-



## የወያኔን እድሜ ለማሳጠርበአንድነት እንሠራለን

በአገራችን ኢትዮጵያ ላይ የተንሰራፋውን ዘረኛና በታኝ ሥርዓት ለመቀየርና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ለማውረድ በተለያየ ጎራ ተከፍለው የሚታገሉ ድርጅቶች ቁጥር ከምንጊዜውም በላይ እየበረከተ መምጣቱ የጎጠኛውን ቡድን እድሜ በማራዘም ረገድ ጉልህ ሚና መጫወቱ አሌ የማይባል ሀቅ ነው።

ወቅቱ የሚጠይቀውና አገራችንና ሕዝባችን ያሉበትን ደረጃ በአንክሮ የተረዳ አገርና ሕዝቡን አፍቃሪ የሆነ ድርጅትም ሆነ ቡድን ቆም ብሎ ሊያስብ የሚገባበት ደረጃ ላይ መድረሳችንን የሚያሳይ ነው።

በመሆኑም ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ካሉበት አዘቅት በማውጣት ሕዝቡ የስልጣን ባለቤት የሚሆንበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የጋራ ትግልና መስዋዕትነት የግድ የሚለን ደረጃ ላይ መድረሳችን፤ የወያኔን ቡድን በሁለገብ ትግል እየተፋለምን ያለን ድርጅቶች ተጣምሮና አንድ ሆኖ መታገል እንዳለብን ካመንን ዓመታት አስቆጥረናል።

በአሁኑ ወቅት ከላይ የጠቀስናቸው ሂደቶች ምላሽ አግኝተው አገራችንና ሕዝባችንን  ከአዘቅት ለማውጣት በመጣመር ብቻ ሳይሆን በውህደት አንድ ሆነን አገራችንንና ሕዝባችንን አንድ በማድረጉ ረገድ አስፈላጊው መስዋዕትነት በመክፈል የትግል እድሜ እናሳጥር በሚል ለውህደት የሚያደርሰንን ውይይት ለመጀመር የሚያስችል ሂደቶችን አጠናቀን ወሳኝ ወደሆነው ሂደት ውስጥ መግባታችንን ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብና ወዳጆች ማብሰር እንፈልጋለን።

**ወደፊት ለመዋሃድ የተስማማነው ድርጅቶች**

1. የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር
2. የግንቦት 7፣ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ
3. የአማራ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ንቅናቄ

ስንሆን በሚኖረው የሽግግር ሂደት ወቅትም በሁሉም የትግል ዘርፍ በጋራ መሥራት የጀመርን መሆናችንን እየገለጽን የመላው ወገናችን ድጋፉ እንዳይለየን ስንል ጥሪዓችንን እናስተላልፋለን።

አንድነት ኃይል ነው !!!

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር -- የግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ -- የአማራ ዲሞክራሲ ኃይሎች ንቅናቄ

## የግንቦት 7 በአለም ዙሪያ የሚያካሄዳቸቸዉን ህዝባዊ ስብሰባዎች ቅድመ ዝግጅት አጠናቀቀ

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በመላው ዓለም ከሚገኙ አባላት፣ ደጋፊዎቹና በአጠቃላይ ከኢትዮጵያውያን ጋር በወቅታዊ አገራዊ ሁኔታዎች ላይ ለመመካከር በ 26 ታላላቅ ከተሞች ያሰናዳቸው ህዝባዊ ስብሰባዎች ቅድመ ዝግጅት በተሳካ ሁኔታ መጠናቀቁን ከድርጅቱ የተላከልን መረጃ ያመለክታል። ህዝባዊ ስብሰባዎቹ በሁሉም የአለም አህጉራት እንደሚካሄዱ የገለጸው ግንቦት 7 በመጭው ረቡዕ ኦገስት 27. 2014 በላስቬጋስ ዩኤስ አሜሪካ ተጀምሮ በሴፕቴንበር 14. 2014 በቤልጂም ብራስልስ በደመቀ ሁኔታ እንደሚጠናቀቅ ገልጿል። ( ወደ ገጽ 3 ዞሯል )

## በመላ አገሪቱ ወጥረት መንገሱን ምንጮቻችን አመለከቱ

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በሚገኙ አንዳንድ ከተሞች ውስጥ የዜጎች እንቅስቃሴ እየተገደበ መምጣቱንና ጸጉረ ልውጥ ሰዎች በአገዛዙ ቅጥረኛ የፌደራል ፖሊሶች በአይነቁራኛ ክትትል እንዲሁም ከፍተኛ ወከባ እየተፈጸመባቸው እንደሚገኝ ምንጮቻችን አመለከቱ። በተለይ በአማራ ክልል ውስጥ በሚገኙት በባህር ዳር፤ ጎንደርና ሌሎችም ከተሞች ላይ በተዘረጉት መንገዶች የሚጠቀሙት የህዝብ መጓጓዣ ተሸከርካሪዎችና መንገደኞች በየ ቅርብ ርቀት ላይ በተኮለኮሉት የፍተሻ ኬላዎች ላይ በተጠንቀቅ በሚባበቁ የአገዛዙ ቅጥረኛ የፌደራል ፖሊሶች ፍተሻ እያደረጉ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል። መንገደኞቹ ማንነታቸው የሚገልጽ የመታወቂያ ደብተር እንዲያሳዩ እንደሚገደዱም ከአካባቢው የደረሰን መረጃ ያሳያል። የአይን እማኞች እንዳመለከቱት ከባህርዳር ወደ ጎንደር ከሚያስኬደው መንገድ ላይ በተተከሉት የአዘዞ፤ የእንፍራንዝ፤ የአዲስ ዘመንና ወረታ የመሳሰሉት የፍተሻ ኬላዎች ላይ የሚገኙት ቅጥረኛ ፖሊሶች ተጓዦችን የመታወቂያ ደብተር እንዲያሳዩ ከመጠየቅ በተጨማሪ ጸጉረ ልውጥ የሆኑ ሰዎችን በመንገዳቸው ላይ ሳይቀር በማስቆም ማንነታቸው እንዲያስረዱ እንደሚጠየቁ ለማወቅ ተችሏል። ዘጋቢያችን ለውጥረቱና ለስጋቱ መንስኤው ምን እንደሆነ ለማወቅ ባደረገው ጥረት በየመን የጽጥታ ሃይሎች ታፍነው ለጠላት ተላልፈው ከተሰጡት የግንቦት 7  ዋና ጸሃፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።

( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ግንቦት 7፤ የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞችና የአማራ ዲሞክራሲያዊ ሃይሎች ንቅናቄ ወደ ውህደት የሚያደርሳቸውን የስምምነት ፊርማ ተፈራረሙ

የፋሽስቱ ወያኔን አገዛዝ ለመገርሰስ በተለያዩ መንገዶች ሲታገሉ የቆዩት 3 ቱ ድርጅቶች ወደ ውህደት የሚያደርሳቸውን የጋራ ስምምነት ፊርማ መፈራረማቸውን ለሬዲዮ ክፍላችን የተላከው መረጃ ያመለክታል። የፋሽስቱ ወያኔን ዕድሜ ለማሳጠር በአንድነት እንሰራለን! በሚል ድርጅቶቹ በጋራ ባወጡት መግለጫ በአገራችን ኢትዮጵያ የተንሰራፋውን ዘረኛና በታኝ ስርአት ከኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ ላይ ለማውረድና ሕዝቦቿን ካሉበት አዘቅት በማውጣት የስልጣን ባለቤት የሚሆንበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የጋራ ትግልና መስዋዕትነት ወሳኝ መሆኑን በማመን አንድ ሆነን አገዛዙን በጠነከረ መንገድ ለመፋለም ተስማምተናል ሲሉ በጋራ የመስራቱን አስፈላጊነት ድርጅቶቹ ገልፀዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ውህደት የፈጸሙት 3 ቱ ድርጅቶች የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር፣ የግንቦት 7፣ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እንዲሁም የአማራ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ንቅናቄ የተጀመረውን የነፃነት ትግል ከግብ ለማድረስ ህዝባዊ ድጋፍ ይደረግላቸው ዘንድ ጥሪ አቀረቡ የፋሽስቱ ወያኔን ዕድሜ ለማሳጠር በአንድነት እንሰራለን! በሚል በሳምንቱ መጀመሪያ ላይ ድርጅቶቹ በጋራ ባወጡት መግለጫ በአገራችን ኢትዮጵያ የተንሰራፋውን ፋሽስታዊ ስርአት ከኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ ላይ ለማውረድና ሕዝቦቿን ከገቡበት አዘቅት በማውጣት የስልጣን ባለቤት ለማድረግ የጋራ ትግልና መስዋዕትነት ወሳኝ መሆኑን በማመን አንድ ሆነን አገዛዙን በጠነከረ መንገድ ለመፋለም ተስማምተናል ሲሉ የውህደቱን አስፈላጊነት የገለፁት ድርጅቶቹ አያይዘውም አስፈላጊውን መስዋዕትነት በመክፈል የጉጅሌው ወያኔን እድሜ ለማሳጠር በምናደርገው እልህ አስጨረሽ የነፃነት ትግል የኢትዮጵያ ህዝብ ከጎናቸው በመሰለፍ ድጋፍ ያደርግላቸው ዘንድ ጥሪያቸውን አቅርበዋል። የነፃነት ቀኑ እየተቃረበ መሆኑን ያመላከቱት የድርጅቶቹ ከፍተኛ አመራሮች የኢትዮጵያ ህዝብ ባለበት ቦታ ሆኖ ትግሉን ማፋፋምና መቀላቀል ይኖርበታል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል። ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ኢትዮጵያ ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የሚሰስልጠና አመጽ ሊቀሰቅስ ይችላል በሚል ፍራቻ ተዉጣለች

የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ የፖለቲካ አጀንዳውን በተማሪው ውስጥ ለማስረጽ እያደረገ ያለው ሙከራ ሙሉ በሙሉ መክሸፉንና በሁሉም ተቋማት እየተሰጡ ያሉ ስልጠናዎች በከባድ ተቃውሞ እየተናጡ እንደሚገኙ ምንጮቻችን አመለከቱ። ይህንኑ ተቃውሞ ተከትሎ ወደ አመጽ ተማሪዎቹ እንዳያመሩ ስጋት ውስጥ የወደቀው አገዛዙ በሰልጣኝ ተማሪዎች ላይ ከፍተኛ ቁጥጥር እየተደረገ ሲሆን በተለይ ከስልጠናዎች መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች ከግቢ እንዳይወጡ መከልከላቸውን ለማወቅ ተችሏል። ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## በድርጅቶች ውህደትና ቅንጅት አገርን ማዳን!!!

ኢትዮጵያዊያንን በዘር እና በሀይማኖት ለያይቶን እርስ በርስ እያጋጨን በመግዛት ላይ ያለውን ወያኔን ለማሸነፍ እና በምትኩም ከራሷ ጋር የታረቀች፤ ፍትህ የሰፈነባት፤ እኩልነት የተረጋገጠባት እና በኃያላን አገሮች እርጥባን ሳይሆን በራሷ አቅም የምትተማመን ጠንካራ ሀገር እንድትኖረን የነፃነትና የዲሞክራሲ ኃይሎት መተባበር እንዳለባቸው ሲነገርና ሲወተወት ቆይቷል። ይሁን እንጂ በህወሓት የከፋፍለህ ግዛው ፓሊሲ እና በፓለቲካ ባህላችን ኋላቀርነት ምክንያት እስካሁን የተደረጉ የትብብር ጥረቶች የተፈለገውን ውጤት ሳያስገኙ ቀርተዋል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ ቀድሞ የተደረጉት ጥረቶች የተጠበቀውን ውጤት አለማስገኘታቸዉ ተስፋ ሳያስቆርጠዉ ከእያንዳንዱ ጥረት ልምድ እየወሰደ የኢትዮጵያዊያን አንድነት እስኪረጋገጥ ድረስ አዳዲስ የትብብር ጥረቶች መደረግ አለባቸዉ ብሎ ያምናል። በዚህም መሠረት የትብብር መርህ ነድፎ ትግል ውስጥ ካሉ ሁሉም የፓለቲካ ድርጅቶች ጋር ሲነጋገር እና ሲደራደር ቆይቷል። እንደሚታወቀው የንቅናቄዓችን አበይት የትብብር መርሆች ሁለት ናቸው። መርህ አንድ፣ ለውጥ እንዲመጣ የምንታገለው ኢትዮጵያ በምትባል አገር ውስጥ መሆኑ ማመን ነው። መርህ ሁለት ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ በሁሉም እርከኖች የመንግሥት ሥልጣን መያዝ የሚገባው በሕዝብ ነፃ ምርጫ ብቻ መሆኑን መቀበል ናቸው።

በምድር ላይ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ከሚያደርጉ ኃይሎች መካከል የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር እና የአማራ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ንቅናቄ ሁለቱንም መርሆዎች የሚያሟሉ ናቸው። እነዚህ ድርጅቶች በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ላይ ከንቅናቄዓችን የተለየ አቋም የላቸውም። በአለፉት ሁለት ዓመታት ድርጅቶቹ ተቀራርበው እንዲሠሩ በመደረጉ ከአመራር አልፎ አባላት መካከል መልካም ወዳጅነት መመሥረት ተችሏል። የነፃነት ትግላችን የደረሰበት ደረጃ እና የድርጅቶቹንም ቅርርብ በመገምገም ሶስቱ ድርጅቶች ማለትም የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር፣ የግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄና እና የአማራ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ንቅናቄ መዋሃዳቸው ትግሉን ያራምዳል ተብሎ ታምኖበታል። በዚህም መሠረት ሶስቱ ድርጅቶች ለመዋሃድ ተስማምተን ስምምነታችንን ይፋ አድርገናል። ድርጅቶቹን የማዋሃድ ዝርዝር ሥራም ተጀምሯል።

ከስትራቴጂ አንፃር የትብብር ጥረታችን በዚህ አያበቃም። በዓላማ የምንቀራረብ ሆኖ የአደረጃጀት ልዩነት ያለን የዲሞክራሲ ኃይሎች ጋር በጥምረት እየሠራን ድርጅቶቻችንን ይበልጥ ለማቀራረብ ጥረት እያደረግን ነው። በዚህ ረገድ ግንባር ቀደም ተጠቃሹ የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ትህዴን) ነው። ንቅናቄዓችን ከትህዴን ጋር ከፍተኛ በሆነ መቀራረብና መተማመን ይሠራል። ይህ መቀራረብና መተማመን ጎልብቶ አንድ የጋራ አመራር የሚፈጥርበት ጊዜ እንዲቀርብ ጥረት እናደርጋለን። ምድር ላይ ከሚገኙ ሌሎች ተመሳሳይ ድርጅቶች ጋርም በመደጋገፍ እንሠራለን። በመጨረሻም ተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ ካሉ ማናቸውም ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ጋር ለመወያየት ዝግጁዎች መሆናችንን ደግመን ደጋግመን እናረጋግጣለን። ልዩነቶቻችንን ማጥበብ ባንችል እንኳን የምንተባበርባቸው መንገዶች ይኖራሉ ብለን እናምናለን።

የጦር ኃይሉንና የስለላ መዋቅሩን ዘረኛ በሆነ መንገድ የገነባውንና የኢትዮጵያን ሀብት በመዝረፍ የደረጀው ህወሓትን ለማሸነፍ ትብብር ወሳኝ ጉዳይ ነው። ከወያኔ አገዛዝ ውድቀት በኋላ ወደ ተረጋጋ ሰላምና ልማት ፊታችንን የምናዞር መሆናችን ዋስትና የሚሰጠን በአንድ ዕዝ የሚመራ የአገር አድን ሠራዊት ማደራጀት ስንችል ነው። የአሁኑ ውህደት የዚህ አገር አገር አድን ሠራዊት ጥንስስ ሊሆን ይችላል ብለን እናምናለን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወያኔ በኋላ የሚመጣው ምን እንደሆነ ባለማወቅ ሥጋት ውስጥ ሊገባ አይገባም። በዋና ዋና የአገሪቱ የፓለቲካ ድርጅቶች ውህደት እና ቅንጅት የተዋቀረ በአንድ ማዕከላዊ አመራር ሥር የሆነ አገር አድን ሠራዊት በተቻለ ፍጥነት ሊገነባ ይገባል።

ሶስቱ ድርጅቶች ለማድረግ በወሰንነው ውህደት የዚህ የአገር አድን ሠራዊት ምሥረታን ጀምረናል። ስለኢትዮጵያ እና ሕዝቧ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ ላለ ማንኛውም የኅብረተሰብ ክፍል ደህንነት ያገባናል የምትሉ ወገኖቻችን ሁሉ በዚህ አገር አድን ሠራዊት ምሥረታ ላይ እንድንነጋገር አበክረን እንጠይቃለን።

የኢትዮጵያ ሕዝብም የትብብሩ መንፈስ አገርን የማዳን ግብ ያለመ መሆኑን በመገንዘብ ከተባበረው ድርጅት ጎን እንዲቆም ጥሪ እናደርጋለን። የፍትህ፣ የእኩልነት፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ጉዳይ የሚያገባው ኢትዮጵያዊ ሁሉ እንዲቀላቀለንና እንዲያግዘን ጥሪዓችንን እናቀርባለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## በመላ አገሪቱ ወጥረት መንገሱን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በተያያዘ ዜና የጉጅሌው ወያኔ የኦሮምያ ክልል የጥፋት ክንፍ የሆነው ኦህዴድ በክልሉ የተፈጠረውን ውጥረት ተከትሎ በየደረጃው ያሉ አመራሮችን አስቸኳይ ስብሰባ መጥራቱን ለማወቅ ተችሏል። በሁሉም የኦሮምያ ክልሎች በሚገኙ ዞኖች ውስጥ የሚገኙ ሹማምንትን፣ የግብርና፣ የሴቶች ጽ/ቤት ፣ መሬት ጥበቃ ፣ ሲቪል ሰርቪስ፣ የኮሚኒኬሽን ጽ/ቤት፣ ውሃና ማእድን፣ ገጠር መንገድ ፣ ጥቃቅንና አነስተኛ ጽ/ቤት ፣ ገንዘብና ኢኮኖሚ ፣ትምህርት/ጽ/ቤት፣ እና የወጣቶችና ስፖርት ሹማምንት በሙሉ ከዛሬ ጀምሮ ለአስቸኳይ ስብሰባ እንዲከቱ መታዘዙ ታውቋል። አስቸኳይ ስብሰባው የተጠራው ህዝቡ በክልሉ የተንሰራፋውን ስርአት አልበኝነትንና በአገዛዙ እየደረሰበት ያለውን ግፍ በመቃወም አደባባይ ሊወጣ ይችላል የሚል ከፍተኛ ስጋት በማየሉ መሆኑን የውስጥ ምንጫችን አመልክቷል።

ግኢንኢ በሌላ ዜና የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ በአገሪቱ የስራ ማቆም አድማ እና የተማሪዎች አመጽ ሊቀሰቀስ ይችላል በሚል ብርክ እንደያዘው ለማወቅ ተችሏል። ጉጅሌዎቹ ከመጭው ምርጫ ተብየ ድራማ በፊት በኢትዮጵያ ውስጥ የስራ ማቆም አድማ እና የተማሪዎች አመጽ ሊቀሰቀስ እንደሚችል አመላካች ሁኔታዎች መታየታቸውን ተከትሎ አገዛዙ ውጥረት ውስጥ መግባቱን ለማወቅ ተችሏል። በተለይ የውስጥ ውጥረቱን ተከትሎ አገዛዙ የመሰንጠቅ አደጋ እንደተደቀነበትም ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በአገዛዙ ሹማምንትና ካድሬዎች ሕዝቡ እንደተማረረ፤ የአገዛዙ ውሸት፤ ሙስና ከፈጠረው የኑሮ ድቀት ጋር ተደማምሮ መጨው ጊዜ ለፋሽስቱ ወያኔ ገሃነም እንደሆነበት ከምንጮቻችን መረጃ ለማወቅ ችለናል። ከቅርብ ጊዜ ወዲም አብዛኛው የአገዛዙ ሹማምንትና ካድሬዎች ጭምር አገሪቱን ለማጥፋት ከቆመው የከፋፋዩና ዘረኛውን ድርጅት ውድቀትን ለማፍጠን በተለይ ለኢትዮጵያ ነፃነት ከሚታገሉ ዲሞክራሲያዊ ሃይሎች ጋር መረጃ መለዋወጥ መጀመራቸውን ለማወቅ ተችሏል

## ኢትዮጵያ ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የሚስስልጠና

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ይህም የተደረገው ተማሪዎቹ ከማሰልጠኛ ጣቢያዎቹ ውጭ ለሚገኘው ህዝብ በተለይም ለሚዲያዎች መረጃ እየሰጣችሁ ነው በሚል እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። ጭንቀት ውስጥ የወደቁት የጉጅሌው ወያኔ ካድሬዎች ተማሪዎቹን «ከማን ጋር እንደምትገናኙ እናውቃለን፡፡ «በፌስ ቡክ ውዥንብር ትነዛላችሁ» በማለት ለማስፈራራትና ለማሸማቀቅ ሙከራ እያደረጉባቸው እንደሚገኝም ታውቋል። በስልጠናዎቹ ላይ ተቃውሞና ትችት የሚሰነዝሩ ተማሪዎች እየተጠሩ ማስፈራሪያና ዛቻ እንደሚደርስባቸው ምንጮቻችን አመልክተዋል።

በተያያዘ ዜና የፖለቲካ ስልጠናውን ተከትሎ በኦሮሚያ ክልል በመቶዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎች መታሰራቸውን ለማወቅ ተችሏል። የምስራቅ አፍሪካ የሰብአዊ መብቶች ሊግ ባወጣው መግለጫ ካለፉት 2 ሳምንታት ጀምሮ በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች የተጀመረውን የፖለቲካ ስልጠና ተከትሎ በአምቦ ዩኒቨርስቲ ከ100 በላይ እንዲሁም ከወለጋ ዩኒቨርስቲ 5 ተማሪዎች ታፍነው መወሰዳቸውን አመልክቷል። ከአምቦ ዩኒቨርስቲ የተያዙ ተማሪዎች ሰንቀሌ እየተባለ ወደሚጠራ እስር ቤት የተወሰዱ ሲሆን ተማሪዎቹ ስለ አገር አንድነት ከመነጋጋር በፊት በቅርቡ ጓደኞቻቸውን የገደሉ የአገዛዙ ቅጥረኛ ፖሊሶች ለፍርድ እንዲቀርቡ መጠየቃቸው ለእስር እንደዳረጋቸው ታውቋል። በፋሽስቱ ወያኔ ታፍነው የተወሰዱት 5 የወለጋ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች እስካሁን ድረስ ያሉበት ቦታ አለመታወቁን የሰብአዊ መብት ሊጉ ገልጿል። በኢሉ አባቦር ዞን ፣ በዶራኒ ወረዳ ፣ ኢሊሞ ቀበሌ ደግሞ ከ10 ቀናት በፊት ከ100 በላይ ሰዎች መታሰራቸውን ተገልጿል። በመጨረሻም የሰብአዊ መብት ሊጉ የጉጅሌው ወያኔ በንፁሃን ዜጎች ላይ እየፈፀመ የሚገኘውን ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰት እንዲያቆም አለማቀፍ የሰብአዊ መብት ድርጅቶችና መንግስታት ጫና እንዲያደርጉ በመግለጫው አመልክቷል።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝ ብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን
የፖስታ ሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916 2003EX Haarlem, The Netherlands

## ኑና እንወያይ

የወያኔ ዘረኞች የግንቦት 7 የፍትህ፤ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ዋና ጸሐፊ የሆኑትን አቶ አንዳርጋቸዉ ጽጌን ፍጹም ህገወጥ በሆነ መንገድ አስሮ ማሰቃየት ከጀመሩ እነሆ ሃምሳ ቀኖች ተቆጥረዋል። ሠላማዊ ዜጎችን ሽብርተኛ ብለዉ ካሰሩ በኋላ የፈጠራ ታሪክ እየጻፉ የቴሌቪዥን ድራማ መስራት የለመዱት ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች በአቶ አንዳርጋቸዉ ላይም በዉሸት የተቀነባበረ ድራማ ሰርተዉ የዚህን ጀግና ሰዉ ተክለሰዉነት ጥላሸት ለመቀባት ሞክረዋል። ሆኖም ቆሻሻ ፈብራኪዎቹ የወያኔ ፕሮፓጋንዳ ተቋሞች ያሻቸዉን ድራማ ቢሰሩም በአለም ዙሪያ የሚኖሩ ኢትዮጵያዉያን በአንድ ድምጽ "እኔም አንዳርጋቸዉ ነኝ" እያሉ ትግሉን በመቀላቀል ግንቦት 7 የዕልፍ  አዕላፍት ድምጽ አንጂ የአንድና የሁለት ሰዎች ድርጅት አለመሆኑን በተግባር ለወዳጅም ለጠላትም አሳይተዋል። በእርግጥም ግንቦት 7 ወያኔ አንዳርጋቸዉን ካሰረ በኋላ ህዝብን ለማታለል እንደሞከረዉ ያበቃለት ድርጅት ሳይሆን ወያኔና ቆሻሻ ስርዐቱ ተጠራርገዉ ቆሻሻ መጣያ ዉስጥ እስካልገቡ ድረስ በየቀኑ እያደገ የሚሄድ ህዝባዊ መሠረት ያለዉ ድርጅት ነዉ።

ዛሬ ኢትዮጵያን ጨምሮ በየአህጉሩ የሚኖሩ ኢትዮጵያዉያን በአካል ሲገናኙም ሆነ በማህበራዊ ሜዲያዎች ሲሰባሰቡ አንድነታቸዉን የሚገልጹበትና የትግል ቃልኪዳናቸዉን የሚያድሱበት ቃል "እኔም አንዳርጋቸዉ ነኝ" የሚል ቃል ነዉ። ባለፉት ሃምሳ ቀኖች በዚህ መልኩ በወያኔና በተላላኪዎቹ ላይ ቁጣዉን ሲገልጽ የሰነበተዉ በዉጭ አገሮች የሚኖረዉ ኢትዮጵያዊ ወያኔን ባስቸኳይ ለማስወገድ በሚቻልበት መንገድ ለመምከርና ለእናት አገሩ ኢትዮጵያ ያለዉን ፍቅር በተግባር ለማሳየት ከፊታችን እሁድ ነኃሴ 24 ቀን እስከ መስከረም 4 ቀን ባሉት ሦስት ተከታታይ እሁዶች በ26 ታላላቅ የአለም ከተማዎች ዉስጥ በአይነቱ ልዩ የሆናና ከዚህ ቀደም ተደርጎ የማያዉቅ ታላቅ ህዝባዊ ስብሰባ ያደርጋል። የእነዚህ "እኔም አንዳርጋቸዉ ነኝ" በሚል መሪ ቃል የተጠሩ ስብሰባዎች ዋና አላማ አንዳርጋቸዉና ከሱ በፊትም ሆነ ከሱ በኋላ ለእናት አገራቸዉ ኢትዮጵያ አንድነት፤ ሠላምና ብለጽግና ሲሉ የታሰሩና የህይወት መስዋዕትነት የከፈሉ ኢትዮጵያዉያን የቆሙለትን አላማ ከግብ ለማድረስ ምን ማድረግ አለብን የሚለዉን ትልቅ ጥያቄ በጋራ ለመመለስ ነዉ። የኢትዮጵያ ህዝብ ለመብቱና ለነጻነቱ የሚያደርገዉ ትግል ወደመጨረሻዉና ፈታኝ ወደሆነዉ ወሳኝ ምዕራፍ ዉስጥ መግባቱን ሁሉም ኢትዮጵያዉ የተገነዘበዉ ይመስለናል፤ ሆኖም በጋራ ለሚደረግ ህዝባዊ ትግል ህዝብ ቁጭ ብሎ በጋራ  ካልመከረበትና ተስማምቶ ለድል የሚወስደዉን ጎዳና በጋራ ካልቀየሰ ትግላችን ወሳኝ ደረጃ ላይ መድረሱን መገንዘቡ ብቻ በራሱ ፋይዳ ይኖረዋል ብለን አናምንም። ስለሆንም በአነዚህ ብዙዎችን አቀራርበዉና አወያይተዉ ለህዝባዊ ትግሉ የሚበጁ ጠቃሚ ሀሳቦችን ያፈልቃሉ ብለን በምናምንባቸዉ ስብሰባዎች ላይ የአገሬ ጉዳይ ከግል ጉዳዩ በላይ ነዉ ብሎ የሚያምን ኢትዮጵያዊ ሁሉ ተገኝቶ የበኩሉን አስተዋጽኦ አንዲያደርግ የዝግጅት ክፍላችን በዚህ አጋጣሚ አገራዊ ጥሪ ያደርጋል።

ለመሆኑ በአለም ዙሪያ የሚኖሩ ኢትዮጵያዉያን ድምጻቸዉን ከፍ አድርገዉ በየአደባባዩና በየስብሰባ አዳራሹ "እኔም አንዳርጋቸዉ ነኝ"  እያሉ ሲጮኹ ምን ማለታቸዉ ነዉ? ወያኔ ስልጣን ይዞ በቆየባቸዉ ባለፉተረ ሃያ ሦስት አመታት ዉስጥ አያሌ ኢትዮጵዉያን የፍትህ፤ የነጻነትና የዲሞክራሲ አርበኞች ታሰረዋል፤ ዘግናኝ በሆነ መልኩ ተገርፈዋል ብዙዎች ደግሞ ተገድለዋል። ኢትዮጵያዉያንን እያፈሱ ማሰር በአንዳርጋቸዉ አልተጀመረም አንዳርጋቸዉ ስለታሰረም አያበቃም። ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች እኛ በቃ ብለን ካላቆምናቸዉ በቀር እኛን ማሰርና መግደል በስልጣን ላይ የመቆየት ዋስትናቸዉ አድርገዉ ስለሚመለከቱ መግደላቸዉንና ማሰራቸዉን በፍጹም አያቆሙም። እንግዲህ "እኔም አንዳርጋቸዉ ነኝ" ስንል ኢትዮጵያ ዉስጥ በዘፈቀደ ዜጎችን ማሰርና መግደል እንዲቆምና አናሳዎች በሀይል የጫኑብን ዘረኛና አግላይ ስርዐት ተደምስሶ ሁሉን አቀፍ ህዝባዊ ስርዐት እንዲፈጠር ማድረግ የምንችለዉን ሁሉ ከማድረግ ወደ ኋላ አንልም ማለት ነዉ። ይህ ማለት ደግሞ አንዳርጋቸዉ ጽጌ፤ እስክንድር ነጋ፤ ኡስታዝ አቡበከር፤ በቀለ ገርባ፤ ሠላማዊት ሞላ፤አዚዛ መሐመድ፤ ርዕዮት አለሙና ሌሎችም ለአገር አንድነትና ለህዝብ ነጻነት ሲታገሉ የዘረኞች ሰለባ የሆኑ ጀግኖቻችን የቆሙለትን አላማ አንግበንና ትከሻ ለትከሻ ተደጋግፈን ወደማይቀረዉ ድል እንጓዛለን ማለት ነዉ።

ዛሬ ሁላችንም በግልጽ እንደምንመለከተዉ ኢትዮጵያዉያን በያሉበት ቦታ ሁሉ ትግሉን እንዴት እንቀላቀል፤ ምን ላድርግ ወይም እንዴት ትግሉን ልርዳ የሚሉ ጥያቄዎችን በየቀኑ እየጠየቁ ነዉ። እነዚህ ጥያቄዎች ደግሞ አንዳርጋቸዉ ስለታሰረ ብቻ ሰኞ ተረግዘዉ ማከሰኞ የተወለዱ ጥያቄዎች ሳይሆኑ በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሆድ ዉስጥ ከሃያ አመታት በላይ ታፍነዉ የቆዩና በአንዳርጋቸዉ መታሰር ፈንድተዉ የወጡ ጥያቄዎች ናቸዉ።

የወያኔ ተላላኪዎች አንደሚከስሱን የአገር ጥላቻ ሳይሆን የአገር ፍቅር ጥያቄዎች ናቸዉ፤ ዘረኝነትና ጎሰኝነት የቀሰቀሳቸዉ ጥያቄዎች ሳይሆኑ ወያኔ ኢትዮጵያ ዉስጥ የዘረጋዉን ያጋጠጠ የዘረኝነት ስርዐት ለማፍረስና በቦታዉ ሁሉንም የአገሪቱ ዜጎች በእኩልነት የሚመለከት ስርዐት ለመፍጠር የሚነሱ ጥያቄዎች ናቸዉ። ግንቦት ሰባት በሃያ ስድስት ከተማዎች ዉስጥ የጠራቸዉ ህዝባዊ ስብሰባዎች እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ ጥያቄዎችን የሚመልሱ ስብሰባዎች ናቸዉ። እነዚህ ስብሰባዎች ከዚህ ቀደም እንደተለመደዉ ከመድረክ ላይ የሚወረወሩ ሀሳቦችን ብቻ አስተናግደዉ የሚበተኑ ስብሰባዎች አይደሉም። እነዚህ ስብሰባዎች የስብሰባዉ አዘጋጆችና የስብሰባዉ ተሳታፊዎች በአንድ መንፈስ ሆነዉ ይህንን የተበታተነ ህዝባዊ ትግል የሚያስተባብርና ትግሉን በተቀናጀ መልክ እንዴት ለድል ማብቃት እንደምንችል የምንመክርባቸዉ ሁሉን አቀፍ ስብሰባዎች ናቸዉ።

በእነዚህ ስብሰባዎች ላይ ወያኔ ግምገማ ወይም ስልጠና እያለ እንደሚያዘጋጃቸዉ መድረኮች ካድሬዎች መመሪያ እየሰጡ ህዝብ ደግሞ ወደደም ጠላ መመሪያዎቹን ተግባራዊ የሚያደርግበት የአንድዮሽ መድረኮች ሳይሆኑ ህዝብ በአገሩ ጉዳዮች ላይ በሚወሰኑ ዉሳኔዎችና በተግባራዊነታቸዉ ላይ ቀጥተኛ የሆነ ተሳትፎ የሚያደርግባቸዉ የሁለትዮሽ መድረኮች ናቸዉ። በሃያ ስድስቱም ከተማዎች ላይ የሚሰበሰበዉ ህዝብ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ምን ይጠበቃል? ከምሁራን ምን ይጠበቃል? ከሴቶች ምን ይጠበቃል? ከወጣቶች ምን ይጠበቃል ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል። የኢትዮጵያ ህዝብ ከወያኔ ዘረኞች ጋር የሚያደርገዉ የሞት ሽረት ትግል በአንድ ምዕራፍ የሚገባደድ፤ በጥቂት ሰዎች የሚሰራ ወይም አንዱ ታጋይ ሌላዉ ገላጋይ ሆኖ የሚታይበት ትግል አይደለም። ይህ ትግል ብዙ ምዕራፎች ያሉት፤ እልፍ አዕላፋት የሚሳተፉበትና ሁሉም የየራሱን አስተዋጽኦ የሚያደርግበት የጋራ ትግል ነዉ። ግንቦት ሰባት ይህንን እዉነታ የሚረዳ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ወደእነዚህ ስብሰባዎች በብዛት በመምጣት በአገሩ የወደፊት ጉዳዮች ላይ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርግ አገራዊ ጥሪ ያስተላልፋል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ**
**እናሸንፋለን!!**

## የግንቦት 7 በአለም ዙሪያ የሚያካሄዳችቸዉን ህዝባዊ ስብሰባዎች . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በእነዚህ ታላላቅ ህዝባዊ ስብሰባዎች ላይ በጠላት እጅ ወድቀው የሚገኙት የንቅናቄው ዋና ፀሐፊ የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ሥራዎች የሚወሱ ሲሆን ፋሽስቱ ወያኔን ማስወገድ በሚቻልባቸው ስልቶች ላይ ሰፊ ውይይት የድርጅቱ አመራሮች ከኢትዮጵያውያን ጋር እንደሚያደርጉ ተገልጿል። ትግላችን ሶስት የትግል ስልቶችን ያስተባበረ ነው ያለው የግንቦት 7 መልዕክት ሕዝባዊ ተቃውሞ፣ ሕዝባዊ እምቢተኝነት እና ሕዝባዊ አመጽ መሆናቸውን በመግለጽ እነዚህን ስልቶች በአገር ውስጥ እና ከአገር ውጭ በተቀናጀ ሁኔታ መተገበር በሚቻልባቸው ሁኔታዎች ላይ የድርጅቱ አመራሮች ከስብሰባው ታዳሚ ኢትዮጵያውያን ጋር ሰፊ ሰአት ወስደው ምክክር እንደሚያደርጉ ለማወቅ ተችሏል። ትግሉ አሁን ወሳኝ የትግል ምዕራፍ ላይ እንደሚገኝ የገለጸው ግንቦት 7 በተለይ በውጭ አገራት የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ከድጋፍ ሰጪነት ወደ ተግባራዊ ተሳትፎ የተሸጋገሩበት ሁኔታን በመጥቀስ ለተቀሩት እስካሁን የትግሉ አካል ላልሆኑ ኢትዮጵያውያን ኑ! ኢትዮጵያ አገራችንን፣ ኢትዮጵያዊ ወገናችንን እና ራሳችን ነፃ ለማውጣት እና በሀገራችን ፍትህና ዲሞክራሲ እንዲሰፍን ለማድረግ በምናደርገው ትግል ተቀላቀሉን ሲል ጥሪ አቅርቧል። በሁሉም የህዝባዊው ስብሰባ ቦታዎች እስከዛሬ ድረስ ንቅናቄውን ለመቀላቀል የተቸገሩ ወገኖችን በትግሉ ለማሳተፍ ይቻል ዘንድ በአባልነትና ደጋፊነት የሚመዘገቡበት መድረክ መመቻቸቱንም ለማወቅ ተችሏል። በተጨማሪም በሁሉም ስብሰባዎች ላይ በረሃ የከተቱት የአርበኛ ወጣቶች ጥረት የሚዘከርበት መድረክ የተመቻቸ ሲሆን ለተቀሩት በአገር ውስጥና በውጭ አገር ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች፤ በሁሉም ደረጃ ለሚገኘው ኢትዮጵያዊ ሁሉ እና ለኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት አባላት ጭምር የጉጅሌው ወያኔን አገዛዝ ለማስወገድ እየተደረገ ያለውን የሞት ሽረት ትግል እንዲቀላቀሉ ጥሪ እንደሚደረግ ለማወቅ ተችሏል።

ክቡራትና ክቡራን አድማጮቻችን የግንቦት 7 የፍትህ፤ የነፃነትና የዲሞክራሲን ንቅናቄ አለማቀፍ ህዝባዊ ስብሰባዎችን በተመለከተ ከየ አህጉራቱ የስብሰባው አዘጋጆችና አስተባባሪዎች ጋር ያደረግነውን ቃለምልልስ ማቅረብ የምንጀምር መሆኑን ለማሳሰብ እንወዳለን። በዚህ አጋጣሚ የሬዲዮ ክፍላችንም በየ አህጉራቱ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን በነዚህ ታሪካዊ ስብሰባዎች በመታደም እየተደረገ ስላለው የነፃነት ትግልና ስለደረሰበት ደረጃ ግንዛቤ እንዲወስዱ፤ በተመቻቸው መድረክ በመጠቀም ትግሉን በአባልነት ወይንም በደጋፊነት በመመዘገብ ድጋፍ እንዲያደርጉ መልዕክቷን ታስተላልፋለች።

………………………………………………………………

## የከፍተኛ የወያኔ ባለስልጣናት የክስ መዝገብ ለስዊድን አለማቀፍ ወንጀል መርማሪ ፖሊስ ተሰጠ

ዘርኛዉ የወያኔ አገዛዝ በ1997ዓም ድምጻችን ይከበር ብለዉ በህጋዊ መንገድ ጥያቄ ያቀረቡትን ከ200 በላይ ኢትዮጵያዉያን በጠራራ ፀሐይ በመትረየስ መጨፍጨፋ የሚታወስ ነዉ። እነዚህ እናት፤ አባትና ልጅ ያለምንም ርህራሄ የጨፈጨፉ አረመኔዎች የሚጠይቃቸዉ ጠፍቶ ሳይሆን ለህግ አንገዛም በማለታቸዉ እስከዛሬ ድረስ ከፍርድ ሳይቀርቡ ቆይተዋል። በቀወርቡ በምርጫ 97 ለተገደሉት እና ለቆሰሉት ፍትህ ለመጠየቅ የተቋቋመው ግብረሃይል ስራውን አጠናቆ ዛሬ የ13ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናትንና የመከላከያ ሰራዊት አዛዦችን ስም ዝርዝር የያዘ የክስ ማመልከቻ ለስዊድን አለማቀፍ የጦር ወንጀል መርማሪ ፖሊስ አስረክቧል። አርከበ እቁባይ፣ በረከት ስምኦን፣ አባ ዱላ ገመዳ፣ ሳሞራ የኑስ፣ አባይ ጸሃየ፣ ጌታቸው አሰፋ፣ ሌ/ጄ ታደሰ ወረደ፣ ሃሰን ሺፋ፣ ሙሉጌታ በርሄ፣ ነጋ በርሄ፣ ወርቅነህገበየሁ፣ ኮማንደር ሰመረ እና አንድ ስሙ ያልተገለጸ ሰው በምርጫ 97 ማግስት ንጹሃን ዜጎች እንዲገደሉ፣ እንዲደፈሩ፣ እንዲታሰሩ፣ ከስራቸው እንዲፈናቀሉና እንዲሰደዱ እንዲሁም አንዳንዶች ታፍነው እንዲወሰዱ ትእዛዝ ሰጥተዋል የሚል ክስ ቀርቦባቸዋል።የክስ ቻርጁ ለፖሊስ መቅረቡን ተከትሎ ቃለ መጠይቅ ያደረግንላቸው ጉዳዩን በማስተባበርና በመምራት ከፍተኛ ሚና የተጫወቱት አቶ ሞላ ይግዛው እንደገለጹት፣የስዊድን አለማቀፍ ወንጀል መርማሪ ፖሊስ በቀረበው የክስ ጭብጥና በቀረቡት የሰነድና የቪዲዮ ማስረጃዎች መርካቱን ገልጿል። ምርመራውን የያዙት ከዚህ ቀደም በዩጎዝላቪያ፣ ሩዋንዳና በሌሎችም አገራት የተፈጸሙትን ወንጀሎች የመረመሩና ከፍተኛ ልምድ ያላቸው ፖሊስ ሲሆኑ፣ እርሳቸውም ለግብረሃይሉ ምርመራውን ዛሬውኑ መጀመራቸውን ማስታወቃቸውን አቶ ሞላ ገልጸዋል።

ስዊድን የኢትዮጵያን ባለስልጣናት ለመክሰስ ምን ስልጣን አላት? የሚል ጥያቄ የቀረበላቸው አቶ ሞላ፣ "የስዊድን ፓርላማ በየትኛውም አገር የተፈጸመ የጦር ወንጀል እና ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰት በስዊድን ፍርድ ቤት እንደሚታይ በቅርቡ መወሰኑ ክሱን ለመመስረት ምክንያት መሆኑን" ገልጸዋል። የስዊድን ፖሊስ ምርመራውን እንዳጠናቀቀ ለአቃቢ ህግ እንደሚያስተላልፍና አቃቢህግም በስዊድን አለማቀፍ የጦር ፍርድ ቤት ክስ እንደሚመሰረት አቶ ሞላ ገልጸዋል።ፖሊስ የሚያካሂደው የምርመራ ውጤት፣ እስካሁን ከተሰባሰቡትና ለወደፊተም ከሚጨመሩት ሰነዶች ጋር ተያይዞ ለተባበሩት መንግስታት የጸጥታው ምክር ቤት እንደሚቀርብና ምክር ቤቱም በአለማፉ የወንጀል ፍርድ ቤት እንዲታይ ትእዛዝ እንዲሰጥ ጥያቄ እንደሚቀርብ ገልጸዋል።

የአሁኑ ክስ በግለሰብ ባለስልጣናት ላይ የቀረበ ቢሆንም፣ ሌሎች ክሶች በተከታታይ እንደሚቀርቡና ክሱ የኢትዮጵያን መንግስት እንደሚያካትት የገለጹት አቶ ሞላ፣ መንግስት በሚከሰስበት ጊዜ በውጭ አገር የሚያንቀሳቅሰው ሃብቱ እንዲታገድ ለማድረግ እንደሚንቀሳቀሱ ተናግረዋል።አሁን የቀረቡት ተከሳሶች 13 ብቻ ቢሆኑም በሂደት እንደሚጨምሩ የገለጹት አቶ ሞላ፣ በወቅቱ በአዲስ አበባ እልቂት ለመፈጸም የመጡት የ34 ባታሊዮን ጦር አዛዦች ስም እንደሚፈለግና የእነዚህን አዛዦች ስም የሚያዉቁ እንዲናገሩ ጠይቀዋል። በኦጋዴን ለተፈጸመው ገድያ እጃቸው አለበት የተባሉ የመንግስት ባለስልጣናትን ለማደን በኢንተርፖል በኩል እንቅስቃሴ መጀመሩንም አቶ ሞላ ፍንጭ ሰጥተዋል። ከ13 ተከሳሾች መካከል የአንደኛው ስም ሆን ተብሎ እንዳይገለጽ መደረጉን አቶ ሞላ ተናግረዋል። የክሱ መመስረት ፍትህ አጥቶ ለቆየው ኢትዮጵያዊ መልካም ዜና መሆኑም አቶ ሞላ ገልጸዋል። ከአቶ ሞላ ጋር የተደረገው ሙሉ ቃለምልልስ ከዜናው በሁዋላ ይቀርባል። ዜናው በኢሳት ሰበር ዜና ከቀረበ በሁዋላ ኢትዮጵያውያን የተለያዩ አስተያየቶችን ስልኮችን በመደወል እየሰጡ ነው።

## የጋዜጣ አዙዋሪዎች ስራ ሊያቆሙ ነው

ሀሳብን በነጻ የመግለጽና የነጻ ሜዲያ ጠላት የሆነዉ የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያ ዉስጥ በህዝብ ተወዳጅ የሆኑ ጋዜጦችንና መጽሄቶችን ባለቤቶች እያሰረ ጋዜጦቹና መጽሄቶቹ እንዳይታተሙ ስለከለከለ ብዙ የጋዜጣ አዟሪዎች ስራ አጥተዉ ከፍተኛ ችግር ላይ መዉደቃቸዉን የአዲስ አበባ ሪፖርተሮቻችን በላከኡልን ዜና ገለጺ። በቅርቡ መንግስት በፋክት፣ አዲስ ጉዳይ፣ ሎሚ፣ እንቁ፣ ጃኖ መጽሄቶችና አፍሮ ታይምስ ጋዜጣ ላይ ፍትህ ሚኒስትር ክስ መመስረቱን ተከትሎ ሚዲያዎቹ ከህትመት በመውጣታቸው ምክንያት ስራ ሊያቆሙ መሆኑን የጋዜጣ አዙዋሪዎች ለነገረ ኢትዮጵያ ገልጸዋል።

በአራት ኪሎ፣ ፒያሳ፣ መርካቶ፣ ሳሪስ፣ ቦሌና ካሳንቺስ የሚገኙ የጋዜጣ አዙዋሪዎች በርካታ አንባቢ የነበራቸው መጽሄቶችና ጋዜጦች ከገበያ በመውጣታቸው፣ ሌሎቹን ጋዜጦችና መጽሄቶች በማዞር ህይወታቸውን መምራት ስለማይችሉ የጋዜጣ ማዞር ስራቸውን አቁመው ሌላ ስራ ለመፈለግ መገደዳቸውን ገልጸዋል፡፡ በተለይ በስርጭት ከአንድ እስከ ሶስት ያለውን ደረጃ ይዘው የነበሩት ፋክት፣ አዲስ ጉዳይና ሎሚን በመሸጥም ሆነ በማከራየት አብዛኛውን ገቢያቸውን ያገኙ እንደነበር የገለጹት የጋዜጣ አዙዋሪዎች አሁን ያሉትን ጋዜጦችና መጽሄቶች በህዝቡ ዘንድ እምብዛም ተነባቢ ባለመሆናቸው በዚህ ስራ ህይወታቸውን መምራት እንደማይችሉ ተናግረዋል፡፡ የፍትህ ሚኒስትር ሚዲያዎቹን ከከሰሰ በኋላ ማተሚያ ቤቶች ቀሪዎቹን ጋዜጦችና መጽሄቶች አናትምም በማለታቸው በርካታ ሚዲያዎች ከገበያ መውጣታቸው ጋዜጣ አዙዋሪዎቹ ስራ እንዲያጡ ምክንያት መሆኑ ተገልጾአል።

አዙዋሪዎቹ በእነዚህ ሚዲያዎች ላይ እርምጃ ከመወሰዱ በፊትም ቢሆን ‹‹የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት በመሆናችሁ የእነሱን አቋም የሚያንጸባርቁ ጋዜጣና መጽሄቶች ለህዝብ እንዲደርስ እያደረጋችሁ ነው፣ ከአጥፊ ኃይሎች ጋር እየተባበራችሁ ነው›› በሚል እርምጃ ይወሰድባቸው እንደነበርና አሁን በመጽሄትና ጋዜጦች ላይ የተወሰደው እርምጃ ሰርተው መኖር እንዳይችሉ እንዳደረጋቸው መግለጻቸውን ጋዜጣው ዘግቧል። ሚዲያዎች በመዘጋታቸው የገቢ ምንጫቸውን ከማጣታቸው በተጨማሪም በሚዲያው ላይ የተወሰደው እርምጃ በእነሱም ላይ የማይወሰድበት ምክንያት እንደሌለ ባለፉት ጊዜያት የደረሰባቸው በደል ማሳያ መሆኑን በመግለጽ ስራውን ሊያቆሙ እንደሚችሉ ገልጸዋል፡፡ ከወራት በፊት ገዥው ፓርቲ የሚቀጥለው ምርጫ ተከትሎ ሚዲያዎች ወደ ክፍለ ሀገር እንዳይደርሱ አከፋፋዮችንና አዙዋሪዎችን በማደራጀት ሚዲያዎችን ከስራ ለማስወጣት እንዳቀደ መገለጹ ይታወቃል።

## የወያኔ መሪዎች የአባይ ወንዝ ግድብን አስመልክቶ ከግብጽና ሱዳን ጋር አስገዳጅ ዉል ተፈራረሙ

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅሞች ላይ ምንግዜም ችግር ያለበት አገር አፍራሹ የወያኔ አገዛዝ የአባይ ወንዝ ግድብን አስመልክቶ ከግብፅ መሪዎች ጋር እስከዛሬ ባደረጋቸዉ ዉይይቶች አልለዉጥም ብሎት የነበረዉን አቋሙን አለዝቦ ለግብፅ ማጎብደድ መጀመሩን ከወደግብፅ የደረስን ዜና አመለከተ። ሰሙኑን የተደረገዉን የግብፅ፤ የሱዳንና የኢትኦጵያን መሪዎች ስብሰባ አስመልክተዉ የግብጽ ጋዜጦች እንደዘገቡት ኢትዮጵያ ለወራት ውድቅ ስታደርገው የነበረውን ስምምነት ከግብጽ ጋርተፈራርማለች። አዲሱ ስምምነት የአባይ ግድብ ግንባታ በውጭ አገር ገለልተኛ አጥኚዎች እንዲጠናና ኢትዮጵያም የጥናቱን ውጤት እንድታከብር የሚያስገድድ ነው።

በኢትዮጵያ መንግስት በኩል ሲደራደሩ የቆዩት የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትሩ አቶ አለማየሁ ተገኑ ከወራት በፊት ሱዳን ላይ ተካሂዶ በነበረው የሰላም ስምምነት ላይግብጽ ግድቡ በውጭ አገር ባለሙያዎች እንዲጠና ያቀረበቻውን አጀንዳ ውድቅ ማድረጓን ገልጸው ነበር። ኢትዮጲያ ግድቡ ከመጀመሩ በፊት በቂ ጥናት እንደተካሄደበት እንዲሁም ገለልተኛ አካል አጥንቶ ችግር እንሌለበት መግለጹን ስታስረዳ ቆይታለች። ይሁን እንጅ ሰሞኑን በተደረገው ውይይት ኢትዮጵያ በፊት የያዘቻውን አቋም ቀይራ በግብጽ አቋም በመስማማት አስገዳጅ ውል ፈርማለች። ውሉ የግድቡ ግንባታ ሳይቋረጥ እንዲካሄድ የሚጠይቅ ሲሆን፣ አዲሱ አጥኚ ቡድን ግድቡ በግብጽ ላይ ችግር ያስከትላል ብሎ ካመነ ኢትዮጵያ የግድቡን ዲዛይን ለመቀየር ትገደዳለች። ኢትዮጵያን ይህን አስገዳጅ ውል ለመፈረም ምን እንዳስገደዳት በግልጽ የታወቀ ነገር የለም።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz

አ<u>ጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## ግንቦት 7፤ የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞችና የአማራ ዲሞክራሲያዊ ሃይሎች ንቅናቄ ወደ ውህደት የሚያደርሳቸውን የስምምነት

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በአገር ቤት፤ በውጭና በጎረቤት አገር የሚኖር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ከድርጅቶቹ ጎን በመሰለፍ የሞራል፤ የገንዘብና የሃሳብ ድጋፍ በመስጠት የዜግነት ግዴታውን እንዲወጣ ጥሪ እንዳቀረቡም ለማወቅ ተችሏል። እየተደረገ ያለው ትግል ሁለገብ ትግል መሆኑን ያመለከቱት ድርጅቶቹ በተለይ በውጭ አገራት እንደተጀመረው ሁሉ በአገር ቤት ውስጥም ህዝቡ በተቀናጀ ሁኔታ ለወያኔ አልገዛም ብሎ እምቢተኝነቱን ማሳየት መጀመር እንዳለበት፤ የወያኔን ንግድ ድርጅቶች የሚያዳክሙ ማንኛውም እምጃዎችን መውሰድ መጀመር እና የፋሽስቱ ወያኔ ካድሬዎችንና ተከታዮችን በማግለል ቅጥረኞቹ እንዲሸማቀቁ ብሎም አገዛዙን ሸሽተው የነፃነት ትግሉን እንዲደግፉ አልያም እንዲቀላቀሉ ማድረግ የሚቻልባቸውን ርምጃዎች በተጠናከረ ሁኔታ መውሰድ መጀመር እንዳለባቸው አ ሳስበዋል።

የድርጅቶቹ ውህደት በኢትዮጵያውያን ዘንድ እየተወደሰ መሆኑንም ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በተለይ ዲሞክራሲያዊ ሃይሎች በጋራ ሆነው መታገል ባለመቻላቸው በተናጠል ያደርጉት የነበረው ትግል ውጤት ባለማምጣቱ አገዛዙ ለ 23 አመታት በስልጣን መቆየት መቻሉን በመግለጽ ይሄ አሁን የተጀመረው ሂደት ይህንን ለወያኔ አገዛዝ የተመቻቸ ትግል ይቀለብሳል በማለት ለነፃነት ናፋቂው የኢትዮጵያ ህዝብ ብስራት መሆኑ በስፋት ተነግሯል። ውህደቱ በሰው ሃይል፤ በእውቀትና በገንዘብ ረገድም ድርጅቶቹን መፈርጠም እንደሚያስችላቸውና የተጀመረውን የነፃነት ትግል ዕድሜ እንደሚያሳጥር በብዙዎች ዘንድ እየተገለጸ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል። በመጨረሻም የኢትዮጵያን አንድነት ያስቀደሙት፤ የህዝቦቿን ነፃነት የሚናፍቁና በሁለገብ የትግል እንቅስቃሴ አገዛዙን ለማስወገድ ውህደት ፈፅመው ኢትዮጵያን ለማዳን የተዘጋጁትን እነዚህን ዲሞክራሲያዊ ሃይሎች በተለይ የመከላከያ ሰራዊቱና አገር ተረካቢ የሆነው ወጣት ትውልድ እንዲቀላቀላቸው ጥሪ ማቅረባቸው ታውቋል።